# ዶሮ ዘወትር ብታልም ጥሬዋን

ዛሬ በዚህች አጭር ጽሁፌ ለመዳሰስ የፈለኩት ቁም ነገር አረዘም ላለ ጊዜ የተረዳሁትና የታዘብኩት ጉዳይ ቢሆንም የአካሄዱን አሳሳቢነት  በቅርብ ከማውቃቸው ጓደኞቼና ቤተሰብ ባሻገር ከሌሎች ጋር ተወያይቼበት አላውቅም ። ነገር ግን ጉዳዩ ከቀን ወደቀን እየገፋ በመምጣቱና አብዛኛው የህብረተሰባችን ክፍል በተለይም በኢትዮጵያ አንድነት አጥብቆ የሚያምነውና የሚከራከረው አውቆትም ይሁን ባለማወቅ አንዳንድ ብልጣብልጥ በሆኑ አፍቃሪ ወያኔና ግንጠላን ለሚያቀነቅኑ የበግ ለምድ የለበሱ ጠላቶቹን ፤ አጥፊዎቹን እየደገፈና ለጠላቱ ስውር ደባና ሰለባ በመሆን ለጸረ አንድነትና ለጸረ ኢትዮጵያዊነት ቡድኖች ከፍተኛ አስተዋጽዖ እያበረከተ እንደሆነም ጭምር ለማስገንዘብ ስለፈለኩ ነው ። ዛሬ የሐገራችን የወደፊት እጣ ፈንታ ከቀን ወደቀን እየደበዘዘና እየጨለመ በመምጣቱ እኔም በሁኔታው ሃዘኔ እጅግ ጥልቅ እየሆነ መጥቷል ፤ ሆድ እየባሰኝም ትእዕግስትም እያጣሁ ስለመጥሁ የግድ ይህንን ዝምታዬን ለኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ባካፍልና ባሳውቅ ምናልባት ጉዳዩን ያልተገነዘበ ካለ እንዲገነዘበው፤ የተገነዘበውም የነገሩን አሳሳቢነት ከወዳጅ ዘመድና ከጓደኛ ጋር እንዲወያዩበትና መፍትሄ እንዲሻ በማለት ነው ።

ሁላችንም እንደምናውቀው የኢትዮ ሚዲያ (Ethiomedia) ድረ ገጽ አዘጋጅ አቶ አብረሃም በላይ ወያኔ ስልጣን ላይ በወጣበት ወቅት የወያኔ ስርአት አገልጋይ እንደነበሩና ከኢትዮጵያዊ ወገናቸው  እጅግ በጣም የራቁ ግለሰብ እንደሆኑ እናውቃለን ፤ አቶ አብረሃም ኩርፊያቸው የጀመረው የአቶ ስዬ አብረሃም ደጋፊ በመሆናቸው እንጂ የሕዝብ ወገን ሆነው እንዳልሆነም ካብዛኛዎቻችን የተሰወረ አይደለም ፤ ድብቁና ለብዙሀኑ ግልጽ ያልሆነው ትግላቸውም መልስን አስወግዶ በስዬ አብረሃም ለመተካት እንጂ ብዙሀኑ ኢትዮጵያዊ እንደሚመኘውና እንደሚፈልገው ሕግና ስራት ፤ እኩልነት ፤ በሐገራችን እንዲሰፍን ለሚደረገው የሞት ሽረት ትግል አኳያ እንዳልሆነ የአደባባይ ሚስጥር ከመሆን በላይ አዋጁን በሚስጥር ካልሆነ በቀር የግለሰቡን አካሄድ ከየት ወዴት እንደሆነ ለእውነተኛው ዴሞክራሲያዊ ስራትን በሐገራችን ለማምጣት ለምንታገል ሐገር ወዳዶች የተሰወረም አልነበረም ፤ ጉዳዩንም ከተገነዘብነው ውለን አድረናል ። አሁን የተቃዋሚው ወገን አጋዥ ፤ ተባባሪና ታላቅ አስተዋጽዖ እንዳበረከቱ እየተደረገ እንደሚነገርላቸው እንዳልሆኑ እንዲያውም በጣም አደገኛ ተልእኮ ያላቸው ከኢትዮ ሪቪው(Ethiorieview)አዘጋጅ ኤልያስ ክፍሌ የበለጠ የሚያሰጉ የውስጥ አርበኛ ናቸው ብል ነገሩን የማጋንን አይመስለኝም ።

የኤልያስ ክፍሌ ዘባራቂነትና በድንቁርና ላይ የተመሰረተ ከኔ በላይ አዋቂ የለም እያለ በተደጋጋሚም ዛሬ አንዱን ሲያሞግስ ነገ ያሞገሰውን ሲሳደብ ፤ ትላንት የሰደበውን እንደገና ዛሬ ሲያወድስ ፤ የትግሉን መስመር ቀያሽ ፤ ከኔ በላይ ላሳር በማለት ያዙኝ ልቀቁኝ በማለት በከንቱ የሚደነፋ አሳዛኝ ፍጡር ነው ። ለተገንጣዩና ላፍራሹ በግልጽ የሚሰጠው ድጋፍ ፤ ከኤርትራው ኢሳያስ የተሰጠውን ተልእኮ ይዞ ስለሚሰራ የሻቢያ ወይም የሰዋ ድረ ገጽ መሆኑ የተጋለጠ ስለሆነ ብዙም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ግለሰብ አይደለም ። ነገር ግን ዋናውና ቁም ነገሩ ህብረተሰባችን  እንደ ኤልያስ በግላጭ የሚታወቁ ብቻ ሳይሆኑ ፋም ኢትዮጵያዊነትን ለበስን ብለው በተቀነባበረ የመሰሪ የአሰራር ዘዴ በማር የተጠቀለለ መርዝን በመርጨት ላይ ያሉትን እንደ አቶ አብረሃም ያሉትን በግልጽ ማንነታቸውን ማስቀመጥና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየሰሩ ያለውን ደባ ማጋለጥ ተገቢ ነው።

የአቶ አብረሃም መለስ ዜናዊን መጥላትና በአንጻሩ ደግሞ ለአቶ ስዬ ያላቸው አድናቆትና ፍቅር ከማንም  የተሰወረ አይደለም ። ያ ማለት ግን የሕዝብ ወገን ናቸው ለማለት እንዳልሆነ ላሰምርበት እወዳለሁ ። አቶ አብረሃም ችግራቸው ከወያኔ ስርአት ጋር ሳይሆን ችግራቸው  ከመለስ ዜናዊ እንደሆነ ግልጽ ነው ። በተደጋጋሚ የግለሰቡን አቋም ጥያቄ ውስጥ እንዳስገባ ያደረጉኝ በርካታ ሁኔታዎች ቢኖሩም አሁን ግን ይህንን ጽሁፍ ለማቅረብ

የገፋፋኝ በቅርቡ (International Oromo Human Rights Conference) በሚል ርዕስ በድረ ገጻቸው ላይ ያወጡት ጉዳይ ነው ፤ ይህንን በድረ ገጻቸው ላይ ሲያወጡ ግለሰቡ የራሳቸው የሆነ ፍላጎትና ለኛም ሊያስተላልፉን የፈለጉት መልእክት  እንዳለ ልንገነዘብ ይገባል ። ግለሰቡ ስለ ኦሮሞ መብት ተሟጋቾች ሕዝባችን ላይ እየደረሰ ያለ ሰቆቃ የሚለውን ለማስተጋባት አይደለም ፤ ዋናው አላማቸው አቶ አብረሃም  ሊነግሩን የፈለጉት ጉዳዩ ሌላ ነው ። የአቶ አብረሃም ቀዳሚ መልዕክታቸው ኦሮሚያ የምትባልም ሐገር እንዳለች ሊያበስሩልን ነው ። ያንንም ሲያደርጉ ኦሮሚያ የምትባለውን አገር እሳቸውና እሳቸውን መሰል ጠባብ ብሄርተኞች ብቻ  የሚያውቋት በዘፈቀደ አይን እስካየ ፈረስ እስከጋለበ የሚመስል ካርታ ጭምርም ጫጭረው አቅርበውልናል ፤ ግለሰቡ ያላቸውን ምኞትና ህልም እሳቸው በዘዴ አስተላለፍኩ ወይም አሳውቅሁ ብለው ሊያስቡ ይችሉ ይሆናል ፤ ሆኖም ግን እኔ የምለው ግን እንደ ፈጣሪያቸው እንደ ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከመናቅ የመነጨ አቀራረብ ነው እላለሁ ፤ ግለሰቡ ዛሬ የትግሬን ጠቅላይ ግዛት ካርታ  ወያኔ እንደ ሞነጫጨረው ከበጌምድርና ሰሜን ከወሎ ጠቅላይ ግዛቶች የተዘረፈውን ትክክለኛው የትግሬ ጠቅላይ ግዛት አካል ነው ወይ ተብለው በአደባባይ ቢጠየቁ ጉሮሮአቸው ውስጥ አጥንት እንደተሰነቀረበት ሲያቃትቱና ሲዘላብዱ እንደማይቀር በድፍረት ለመናገር እችላለሁ ። እኚህ ግለሰብ የኦሮሚያን ካርታ በማሳየትና የኦሮሞ ተገንጣይ ቡድን አጋር መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን ሊነግሩን የፈለጉት ወደዳችሁም ጠላችሁም ኢትዮጵያ የምትባል አገር አላውቅም ፤ ኢትዮጵያ የምትባልም አገር የለችም ነው ያሉን ። አላሉም ልትሉኝ ትችሉ ይሆናል ፤ አዎ !  ለዚህ ነው እኚህ ግለሰብ ከኤልያስ ክፍሌ የበለጡ ብልህና የሚሰሩትን የሚያውቁ አደገኛ ሰው ናቸው የምለው ። በእርግጥ ቃል በቃል እኔ ከላይ እንዳቀረብኩት አላስቀመጡት ይሆናል ሆኖም ግን ያም ቢሆን አላሉም ለማለት አያስደፍርም ፤ በተዘዋዋሪ መንገድ ወደድንም ጠላን ተቀበልንም አልተቀበልን ያንን ነው ያሉን ። ይሄው ለተገንጣዮች ህልም መሳካት የሚያለቅሱት አቶ አብረሃም በላይ ከላይ ባነሳሁት ኦሮሞን እንወክላለን በሚሉ ቡድኖችን በሚመለከት "ኦሮሞ አሜሪካንስ" በሚል ዝባዝንኬ አስነብበውናል ። ወገኖቼ ኦሮሞ አሜሪካንስ የሚባል ነገር የለም ፤ አቶ አብረሃም በላይ ይህንን በማለትና ህበረተሰቡ እንዲያነበው ሲያደርጉ ሊያለማምዱንና ሊያስጨብጡን የፈለጉት የግላቸው ጥብቅ ጉዳይ ስላላቸው ነው ። እሳቸው በኢትዮጵያ ሉአላዊነትና አንድነት ስለማያምኑ ፤ ስውር ተልእኮ ስላላቸውና እርሳቸውም ነገ "ትግሬ አሜሪካን" ብለው እራሳቸውን ሊጠሩ እንደተዘጋጁ ነው ሊነግሩን የፈለጉት ። አቶ አብረሃም በዓለማችን ላይ አንድም ሐገር እንኳን ማወቅ ቀርቶ ስሙንም እንኳን ሰምቶት የማያውቀውን ኦሮሚያ እርሳቸው እውቅና በመስጠት ከወያኔው ፈጣሪያቸው ያልተናነሰ ንቀታቸውን ለኢትዮጵያውያን ሲያሳውቁ ትዕቢታቸው አብጦ  ሊፈነዳ እንደቀረበ ያመላክተናል ። ከእባብ እንቁላል እርግብ አይፈለፈልምና ቀድሞውንም አካሄዳቸውን ለተገነዘብንና ላወቅናቸው ሊደንቀንም ሆነ ሊገርመን አይገባም ። ሆኖም ግን በየዋህነት የግለሰቡን ውስጣዊ ፍላጎትን ምኞት ካልተገነዘበ በቀላሉ ሰው ሊያስት ይችላልና የግድ ማጋለጥ ስላለብኝ ነው ።

ይህ አይነት የአቀራረብና ዘዴያቸው አዲስ አይደለም ፤ ዛሬም አልተጀመረም ይህም የመጨረሻቸው አይሆንም በዚሁና መሰል አቀራረብ የተቻላቸውን ያክል አላማቸው ግቡን እስከሚመታ እንደሚቀጥሉበት እሙን ነው ፤ ድሮም እሳቸውና መሰሎቻቸው አብረውን ይበሉ ይጠጡ የነበሩት ፤ ትምህርት ቤት አብረውን ይሄዱ የነበሩት ፤ ኳሱን በየሰፈራችን አብረውን ይራገጡ የነበሩት ፤ ሀዘናቸው ሀዘናችን ፤ ደስታቸው ደስታችን ሆነን በጥሩ ወንድማማችነት ስንኖር የነበርነው  አይደል እንዴ ዛሬ ከደረስንበት እንድንበቃ ያደረጉን? እኛ በየዋህነትና በወንድምነት ልባችንን ሰደን ወንድሜ ወንድሜ እያልን በራችንን ብርግድ አድርገን ከፍተን ስናስገባቸው እነሱ ግን በጸሀይ እኛን መስለው በጨለማ ከመሰሎቻቸው ጋር ሲገናኙ ግን እንዴት እኛን እንደሚያጠፉ ይመክሩና ይዘክሩ ነበር ፤ እኛም አጥፊያችንን ባለማወቅ ለማንም ልዋጭ ልዋጭ እያለ ለሚለው ሁሉ በጅ አዙር ገንዘባችንን ከሐገራችን ማፍረሻ ያደረጉትን እነኚህን ጉዶች ባለማወቅ ዛሬ ከደረስንበት ውድቀታችን ታላቅ አስተዋጽኦ ስናደርግ መቆየታችን የትላንት እና የቅርብ ፤ የማይረሳ ጥቁር ትዝታችን ሳያንስ፤

ዛሬም በነ አብርሃም በላይና መሰሎቻቸው  እንደ እቃ ልዋጭ ሲጫወቱብን ችግሩን አለማየትና ወዴትስ እየወሰዱን እንደሆነ ማጤን አለመቻላችን እጅግ ያሳዝናል ።

በኢትዮጵያዊነት ሥም ኢትዮጵያን እያፈረሱ ለኢትዮጵያ አንድነት እታገላለሁ ወያኔን እቃወማለሁ እያሉ መዘመር የማይችሉበት ደረጃ ላይ እንደደረሱና እውነታው ሲጋለጥ ዛሬ ጸረ ወያኔ መሆናቸው ቀርቶ አፍቃሪ ወያኔ መሆናቸውን ሰሞኑን ደረታቸውን ነፍተው በግላጭ ወጥተዋል ፤  በግላጭ መውጣታቸው ባያስደንቀንም ለተመልካችና ላንባቢያን ግን ግልጽ መሆኑ በጣም ደስ ብሎናል ።  ያንድነትና የጸረ ወያኔ ኃይሎችን ድምጽ የሚያስተጋቡ ማንኛውም ድረ ገጾችም ሆኑ ሚዲያዎች ካንድነት ኃይሉ ወገን መቆማቸውና ደጋፊነታቸውን የሚያስመሰክሩት የዚያም አካል መሆናቸውን የሚያረጋግጡት በኢትዮጵያዊነት ቆመው ጠላትን ጠላት ፤ ወዳጅን ወዳጅ ሲሉ ነው ። ወያኔን የሚያሞካሽ ወያኔን አትንኩት ፤ አትውቀሱት ፤ አትንቀሱት እያሉ ጸረ ወያኔ መሆን አይቻልም ። ይህን ስንል ባሉባልታ ሳይሆን ሰሞኑን በድረ ገጻቸው ላይ ያወጡት ወያኔን ማዋረድ አቁሙ "Let the Woyane-bashing end " የሚለው ጽሁፍ ከመረቁ አውጡልኝ ከሥጋው ጾመኛ ነኝ ከማለት ባሻገር ሌላ ትርጉም ሊኖረው አይችልም ። ይሄን ያየ ኢትዮ ሚዲያ በእውነት ከአንድነት ኃይሉ ከኢትዮጵያውያን ወገን ጋር የቆመ ነው ወይስ ከጸረ አንድነቱ ኃይል ከወያኔ ጋር የቆመ ነው? ይሄንን መልሱን ለአንባቢያን እተወዋለሁ።

ከብላቴን ጌታ መርቆርዮስ